Funded by
The European Union

Lead agency

In Partnership with

# ሀገር በቀል፡ አነስተኛና ጀማሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን አቅም በማጎልበት ነጻነታቸውንና ተዓማኒነታቸውን በማረጋገጥ በመልካም አስተዳደርና ሃገራዊ ልማት ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የማስቻል ፕሮጀክት

## አባሪ/ዕዝል/ 3

## የፍላጎት መግለጫ (ኢኦአይ) ማመልከቻ ለማቅረብ የተዘጋጀ መመሪያ

ሰኔ 2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

## መምሪያ/ትእዛዝ/

ይህ መመሪያ የፍላጎት መግለጫ (ኢ ኦ አይ) ለማቅረብ እንዲሁም ለማዘጋጀት ዋነኛ ማጣቀሻ በመሆን የሚያገለግል ነው፡፡ እያንዳንዱ አመልካች ወይም የሲቪል ማህበረሰብ ማመልከት ከመጀመሩ በፊት በዝርዝር የተቀመጡትን የመመሪያውን ክፍሎች በጥልቀት ማየት፡ መገምገም እና ሁሉንም መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

**የማመልከቻ ሂደት**

1. ሁሉም አመልካቾች ማመልከቻቸውን በአባሪ/እዝል 2 በተቀመጠው ቅጽ መሰረት ማዘጋጀት እና ሌሎችን የሲቪል ማህበረሰቡ ህጋዊ ሰነዶች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. የብቁነት መስፈርቶች/ማረጋገጫ፡ ይህ ሁሉም አመልካቾች አስገዳጅ የብቁነት መስፈርቶችን ማሟላታቸውና እና አለማሟላታቸው የሚረጋገጥባቸው መለኪያዎች ናቸው፡፡ እነዚህን አስገዳጅ መስፈርቶች የማያሟሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ወደሚቀጥለው ዙር አይሸጋገሩም፡፡
3. ፕሮፖሳል ዝግጅት፡ በዚህ ዙር የፍላጎት መግለጫ ካቀረቡ አመልካቾች መካከል ባስመዘገቡት ውጤት መሰረት የተወሰኑት ብቻ ተለይተው በየክልሉ የሚሰጡ የፕሮፖሳል አዘገጃጅት ስልጠና የሚሳተፉ ይሆናል፡፡ በስልጠናው የማይሳተፉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለፕሮፖሳል ዝግጅት አይጋበዙም፡፡

በዚህ ግራንት ዙር ለመወዳር ሁሉም አመልካቾች ይህንን መመሪያ በጥልቀት ሊገመግሙ እና መስፈርቶቹን እንዲሁም የማመልከቻ ሂደቱን በሚገባ ሊገነዘቡ ፣ መመሪያው ላይ የተቀመጡትን አስገዳጅ መስፈርቶች በጥንቃቄ መመልከትና ያስገዳጅነት መሰፈርቶችን ሙሉ በሙሉ ማሟላታቸውንና ብቁነታቸውን ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡ ማንኛውም የዚህ ሰብግራንት አመልካች አባሪ/እዝል 2 ን በጥንቃቄ በመሙላት ትክክለኛና የተደራጀ መረጃ መስጠት ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሁሉም አመልካቾች የማረጋገጫ ፎርሙን (ድክላሬሽን) በመሙላት፡ በመፈረምና የድርጅታቸውን ማህተም በማድረግ የግራንቱን መመሪያ በአግባቡ መረዳታቸውንና የሰጡትን መረጃ ትክክለኛንት ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**ከዚህ በተጨማሪ፡**

- ሁሉም አመልካቾች ሁሉንም የማመልከቻ ሰነዶች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ብቻ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ትክክለኛ ያልሆኑ ወይም ያልተሟሉ የፍላጎት ማመልከቻዎች በቀጥታ ከግራንት ውድድር ሂደቱ ወጭ ያስደርጋሉ፡፡
- አመልካቾች ያላቸውን ጥያቄዎች ወይም ተጨማሪ ማብራሪያዎች ከሚመለከታቸው የፕሮግራሙ ተወካዮች ማግኘት ይችላሉ፡፡

## ማውጫ


መምሪያ/ትእዛዝ/ .................... 2

ማውጫ .................... 3

1. የኢ.ዩ. ሲ. ኤስ. ኤፍ ፐላስ ፕሮጀክት ዳራ .................... 4

2. የሰብ ግራንት አቀራረብ ዘዴ እና ሂደት .................... 4

3. የፕሮግራሙ አላማዎች .................... 5

4. ቅድሚያ የሚሰጣቸው የፕሮግራሙ ዘርፎች .................... 6

4.1. የፕሮግራሙ ቁልፍ የትኩረት ዘርፎች .................... 6

5. ባለ ፈርጀ ብዙ ጉዳዮች (Cross-cutting issues) .................... 8

6. የፍላጎት መግለጫ ጥሪ ማሳወቂያዎች እና የመረጃ ክፍለ ጊዜዎች .................... 9

7. ለፍላጎት ማመልከቻ ጥሪው የቀረቡ መስፈርቶች እና ደንቦች .................... 10

7.1. ለፍላጎት መግለጫ ብቁ የሆኑ ድርጅቶች የምርጫ መስፈርቶች .................... 10

7.2. አመልካቾች ሊያሞሉ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች /መስፈርቶች/ .................... 15

7.3. የሚፈቀዱና የማይፈቀዱ ተግባራትና ወጪዎችን በሚመለከት፡ .................... 16

7.4. የማመልከቻ ሒደቶች እና የጊዜ ገደብ .................... 19

7.5. የማመልከቻዎች ግምገማ ሥርዓት .................... 21

7.6. የፍላጎት መግለጫ አስተዳደራዊ ግምገማ .................... 21

7.7. የፍላጎት መግለጫ ዝርዝር ግምገማ .................... 22

## 1. የኢ.ዩ. ሲ. ኤስ. ኤፍ ፕላስ ፕሮጀክት ዳራ

የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ ፕላስ (ሲ. ኤስ. ኤፍ ፕላስ) ፕሮግራም በአውሮፓ ህብረት (ኢ.ዩ.) የኢትዮጵያ ልኡክ አማካኝነት በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች (ሲ.ኤስ.ኦ.) ዘርፍ ፕሮግራም የበርካታ አመታት የድርጅት መርሀግብር (ማፕ) 2021-2024 ክፍል ነው:: በዚህ መርሀግብር መሰረት ክርስቲያን ኤይድ ከአውሮፓ ህብረት ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ የሲቪል ማህበረሰብ የአቅም ግንባታ  ማጠናከሪያ ፕሮግራም እንዲተገብር ስምምነት ወስዷል፡፡ ፕሮግራሙ “ሀገር በቀል፡ አነስተኛና እና ጀማሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን አቅም በማጎልበት ነጻነታቸውንና ተዓማኒነታቸውን በማረጋገጥ በመልካም አስተዳደር እና ሃገራዊ ልማት ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የማስቻል ፕሮጀክት” ወይም (“ኢ.ዩ.ሲ.ኤስ.ኤፍ ፕላስ ”) ወይም  (“ሲ.ኤስ.ኤፍ ፕላስ) በመባል የሚጠራ ነው::

*ሲ.ኤስ.ኤፍ ፕላስ* የ4 አመት በአውሮፓ ህብረት የገንዘብ ድጋፍ የሚደገፍ ፕሮግራም ሲሆን ዋነኛ አላማውም የሀገር ውስጥ፡ አነስተኛና እና ጀማሪ ደረጃ ላይ የሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በማእከላዊ ኢትዮጵያ ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ ፣ ትግራይ ክልሎችና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚተገብር ፕሮግራም ነው፡፡ ፕሮግራሙ ከየካቲት 2018 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥር 2021 ባሉት ጊዜያት የሚፈጸም ሲሆን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አቅማቸው አንድጎለብትና ተደራሽነታቸው እንዲያድግ በማስቻል በመልካም አስተዳደር እና ልማት ስራ ላይ ንቁ ተሳታፊዎችና ተአማኒነት እንድኖራቸው መስራት ነው:: ክርስቲያን ኤይድ ፕሮግራሙን የሚተገብረው ከሲቪል ሶሳይቲ ሪሶርስ ሴንተር (ሲ ኤስ አር ሲ) ፣ ጩራ አቡጊዳ ኪነ ጥበባዊ ማህበር (ሲ ኤ ኤ ኤ) እና ከኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጊቶች ፎረም (ኢ ሲ ኤስ ኤፍ) ጋር በጋራ በመሆን ነው፡፡

ፕሮግራሙ ሀገር በቀል፡ አነስተኛና እና ጀማሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችንና ጀማሪ ኔትወርኮች ላይ ትኩርት በማድረግ በሶስተኛ ወገን ፋይናንሲንግ (ሰብ ግራንቲንግ) እና እቅም ግንባታ ስራዎች በማጠናከር በትክክለኛ መረጃ ላይ የተደገፈ የፖሊሲ ወይይትና ክርክር በሁሉም የመዋቅር ደረጃዎች (ከዝቅተኛ አእስከ መካከለኛ ብሎም ከፍተኛ) በማድረግ ሊምግቱ የሚችሉበትን አቅም መፍጠር ነው:: የፕሮግራሙ ዋነኛ ትኩረቶች አነስተኛ ፣ ባማደግ ላይ ያሉና በታችኛው የአርከን ደረጃ የሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ደረጅቶቸ፡ ኔትወርኮቸ፡ ጥምረቶች፡ ማህበሮች እንዲሁም ሌሎቸ ሲሆኑ ተጋላጭ ለሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችት ተደራሽ ከማድረግ አኳያ በኢኮኖሚ አቅም ግንባታ፡ በመልካም አስተዳደር፡ በዲሞክራሲ፡ በሰላምና ደህንነት፡ በሰብአዊ መብቶች፡ በክልል፡ በዞንና በወረዳ ደረጃ እንድሰሩ ማስቻል ነው፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች  ተደራሽ ያልሆኑ ደርጅቶቸ ቢሆኑም በኢትዮጵያ ምቹ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሁኔታ(ከባቢ) ከመፍጠር አንጻር የሚኖራቸው ሚና ቀላል የሚባል አይሆንም ፡፡

## 2. የሰብ ግራንት አቀራረብ ዘዴ እና ሂደት

ይህ ሁለተኛው የፍላጎት መግለጫ (ኢ.ኦ.አይ) በድምሩ 20 የሚሆኑ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን (በእያንዳንዱ ክልል 5 ደርጅቶች) ለመምረጥ የወጣ ማስታወቂያ ነው፡፡ በዚህ ዙር የሚመረጡት ደርጅቶች ሁሉን አቀፍ የሆነ የአቅም ማጎልበቻ እና የሶሰተኛ ወገን ፋይናንስ ድጋፍ ከ12-18 ወራት ለሚሆን የጊዜ ቆይታ የሚያገኙ ይሆናል፡፡

የፍላጎት መግለጫ አመልካች ድርጅቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታዎችና የመምረጫ መስፈርቶች በዚህ መመሪያ ክፍል 7 ላይ በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡ ቀደም ብለው የተዘጋጁና ግልጽ የሆኑ የመምረጫ መስፈርቶችን በመጠቀም 40 የሚሆኑ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች (ከእያንዳንዱ ክልል 10) ለፕሮፖዛል ዝግጅት ስልጠና የሚመረጡ ይሆናል፡፡ ስልጠናውን በትኩረት ተሳትፈው ያጠናቀቁ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለፕሮፖዛል ዝግጅት የሚጋበዙ ይሆናል፡፡ በመሆኑም አስር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከትግራይ ፣ አስር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከደቡብ ኢትዮጵያ ፣ አስር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከማእከላዊ ኢትዮጵያ እና አስር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከአዲስ አበባ ለፕሮፖሳል ዝግጅት ሰልጠናና ጽሁፍ የሚመረጡ ይሆናል፡፡ በሁሉም ዙሮች በሲቪል ማህረበሰብ ድርጅቶች መካከል የሚደረጉ ውድድሮች ክልላዊ ውድድሮች ናቸው፡፡ በመጨረሻም በክርስትያን ኤይድና አጋር ድርጅቶች የድርጅታዊ አቅም ዳሰሳ ግምገማ ከተደረገ በህዋላ ከ20 የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር የአጋርነት ስምምነት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## 3. የፐሮግራሙ አላማዎች

የፕሮግራሙ አጠቃላይ አላማ ሀገር በቀል: አነስተኛና በማደግ ላይ ያሉ በማእከላዊ ኢትዮጵያ ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ እና ትግራይ ክልሎች እንዲሁም አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አቅማቸው የጎለበተ ምቹ ሁኔታ የተፈጠረላቸው በመልካም አስተዳደር እና ሃገራዊ ልማት ውጤታማና ተአማኒ ተዋናዮች እንድሆኑ ማስቻል ነው፡፡ ፕሮግራሙ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡

***ዝርዝር አላማ እንድ:*** ሀገር በቀል፡ አነስተኛና በማደግ ላይ የሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን (በተለይም የሴቶች፣ ወጣቶች እና የአእካል ጉዳተኞች) አቅም በሶስተኛ ወገን ፋይናንሲንግና የድርጅት ተኮር የአቅም ማሳደጊያ ድጋፎችን በማድረግ ማጠናከርና በፖሊሲ ውይይት፣ ሞጋችነትና የልማት እቅድ ክትትል እንቅስቃሴዎችን ከአካባቢ/ወረዳ/ እስከ አገር አቀፍ ድረስ እንዲያደረጉ ማስቻል፡፡

***ዝርዝር አላማ ሁለት:*** ሀገር በቀል፡ አነስተኛና በማደግ ላይ ያሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን እዲሁም ኔትዎርኮች (በተለይም ሴቶች፡ ወጣቶች ወይም የአካል ጉዳተኞች) ላይ በማተኮር የኔትዎርኪንግና ትብብር አቅማቸውን በማሳደግ በመካከላቸው የእዉቅት ሽግግር አንድኖር ማድረግ፡ የመንግስት የልማት እቅዶችን/አስራሮችን/ በውጤታማነት መከታተል አንድችሉ ማድረግና የሲቪል ሶሳይቲ ስፔስ (ምቹ ሁኔታ) አንድፈጠር ማስቻል ነው፡፡

እነዚህን አላማዎች ለማሳካት ፕሮግራሙ በቀጥታ ስልሳ ሀገር በቀል፡ አነስተኛና በማደግ ላይ ያሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን፡ ኔትዎርኮችንና ሌሎችንም ማህበራት በሶስተኛ ወገን ፋይናንሲንግ እንዲሁም ፍላጎት ተኮረ የሆነ የአቅም ማጠናከሪያ ድጋፎችን በማቅረብ በቀጥታ የሚሰራ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ፕሮግራሙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶ አካባቢያዊ የሆኑ ከፕሮግራሙ አላማ ጋር የተቆራኙ ተግባራትን በተናበበ መልኩ እንዲሰሩ ያስችላል፡፡ ከአጠቃላይ የፕሮጀክት በጀቱ ውስጥ 2,200,000 ዩሮ በቀጥታ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሶስት ዙሮች የሚተላለፍ ሲሆን፡ 350,000 ዩሮ ለአቅም ማጠናከሪያ/ማጎልበቻ የሚዉል ሲሆን 90,000 ዩሮ ደግሞ ኔትዎርኮችን ለማቋቋምና ለማጠናከር የሚውል ይሆናል፡፡

## 4. ቅድሚያ የሚሰጣቸው የፕሮግራሙ ዘርፎች

የአውሮፓ የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ ፐላስ (ኢ.ዩ. ሲ. ኤስ. ኤፍ ፐላስ) ፕሮግራም ለዚህ የፍላጎት ማቅረቢያ መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ የትኩረት ዘርፎችን በሁሉም ክልሎች በተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች ለይቷል፡፡ አመልካች የሲቪል ማህበረስብ ድርጅቶች የግዴታ መስፈርቶችን ከማሟላት በተጨማሪ የድርጅታቸው ስትራቴጂያዊ ተልዕኮ በፕሮግራሙ ከተለዩት ዘርፎቸ ጋር ቁርኝት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ማንኛውም አመልካች የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት አንድ የፍላጎት ማቅረቢያ ብቻ ማቅረብ ይኖርበታል፡ የሚያቀርበው የፍላጎት መግለጫ በአንድ ዘረፍ ላይ መሆን ይኖርበታል፡፡ ሌሎች መሟላት የሚገባቸውን የግደታ መስፈርቶች በተመለከተ በዚህ ሰነድ ክፍል 7.1 ላይ የተመለከተውን በዝርዝር ማየት ያስፈልጋል፡፡

ሁሉም የፍላጎት ማቅረቢያ ሰነዶች ከተሰበሰቡ በኋላ አመልካቾች የግዴታ መስፈርቶችን ማሟላታቸውንና አለማሟላታቸው ይረጋገጣል፡፡ የግዴታ መስፈርቱን የሚያሟሉ አመልካቾች ብቻ ወደ ቴክኒካዊ አሰሳ/ግምገማ/ የሚያልፉ ሲሆን በክልል ደረጃ ከተወዳዳሪያቸው ጋር ሲነጻጸሩ የተሻለ ውጤት ያመጡ 10 ድርጅቶች ለሮፖዛል ዝግጅት የሚረዳ የ 3 ቀን ሰልጠና እንድሳተፉ የሚጋበዙ ይሆናል፡፡ በመቀጠልም ወደ ፕሮፖዛል ዝግጅት የሚሄዱ ይሆናል፡፡

### 4.1. የፕሮግራሙ ቁልፍ የትኩረት ዘርፎች

#### 4.1.1. ***የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምቹ የሥራ አካባቢ መፍጠር እና የሲቪክ ምህዳርን መጠበቅ***

በዚህ ዘርፍ ትኩረት ተሰጥተው ሊሰሩ የሚችሉ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡-

- የአጋር አካላት ውይይቶችን በተለያዩ ህጎች ዙሪያ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ለመንግስት አካላት ማድረግ/ማመቻቸት
- በአድቮኬሲ ስትራቴጂ እና በተግባቦት ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት
- በሲቪክ ስፔስ ዙሪያ ጥናታዊ ጽሁፎችን ማድረግ፡ በአድቮኬሲ፣ በፖሊሲ ትብብር፡ በኔትዎርኪንግ ትብብር ዙሪያ መስራት
- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለውጥ/ሪፎርም/ ዙሪያ መስራት
- ተከታታይ ውይይቶችን በሲቪክ ስፔስ ፕሮቴክሽን (የሲቪል ማህበረሰብ ጥበቃ) ዙሪያ መስራት

#### **4.1.2. መልካም አስተዳደርና እና ማህበራዊ አካታችነት**

በዚህ ዘርፍ ስር ሊካተቱ የሚችሉ ዋናዋና ተግባራት የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ

- በማህበረሰቡና በመንግስት መካከል የሚደረጉ ውይይቶችን ማድረግ/ማመቻቸት፡ የዜጎችን ንቁ ተሳትፎ ማሳደግና ምቹ መደላድሎችን መፍጠር
- በህዝብ አገልግሎትና በተቋማት ዙሪያ የሚከናወኑ ተግባራትን መቆጣጠር የሚያስችል የማህበረስብ የክትትል መንገዶችን ማመቻቸት/መደገፍ/
- የግልጸኝነትና ተጠያቂነት አሰራሮች እንድኖሩ ማስቻል(ምሳሌ፡ በበጀት አጠቃቀምና በሃብት አመዳድብ)

- የአካታችነት ፖሊሲን አስመልክቶ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ድምጽ ትኩረት እንዲያገኝ ቅዲሚያ ሰጥቶ መስራት

### 4.1.3. *የወጣቶችን ድምጽ እና ውክልና ማጎልበት*

- ወጣቶች ከተለያዩ አካላት ጋር ተከታታይ የፖሊሲ አድቮኬሲ ውይይቶችን እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታዎችን/መደላድሎችን መፍጠር
- ወጣት መር የሆኑ የፖሊሲ አድቮኬሲ ስራዎችና በወጣቶች የስራ እድል/ቅጥር ለመስራት የሚያስችሉ ተግባራት ላይ ትኩረት መስጠት
- በወጣቶች አመራር ዙሪያ የማጣከር ስራዎችን መስራት
- ሁሉን አቀፍ የሆኑና የተቀናጁ ተግባራትን ማከናወን፡፡ ለምሳሌ፡- በትራውማ፣ በግጭትና ፍልሰት ዙሪያ አስፈላጊ የማስገንዘቢያ ስራዎችን በመስራት ሁሉ አቀፍና ቀጣይነት ያላቸው ተግባራትን ማከናወን
- በታችኛው መዋቅር ያሉ የወጣት ማህበራት ላይ ትኩረት ያደረጉ እቅዶችን መተግበርና ስራዎችን መስራት
- ወጣት መር/ተኮር/ የሆኑ የአካባቢ የሰላም ግንባታ እና የሲቪል ማህበረሰብ ስራዎችን መደገፍ

### ***4.1.4. በግጭት አፈታት፣ የሰላም ግንባታ ፣ ማህበራዊ አንድነትን መፍጠርና ህገወጥ ፍልሰትን መከላከል ዙሪያ***

- በስራ ላይ ያሉ የሰላም ግንባታ መዋቅሮችን ማጠናከር
- ማህበረሰብ አቀፍ የሆኑ የሰላም ግንባታ መድረኮችን ማዘጋጀት
- ማህበረሰብ ተኮር የሆኑ የግጭት መከላከያ ዘዴዎችን ያለውን መዋቅር ተጠቅሞ መተግበር
- ሰፋፊ የሆኑ የሰላም ግንባታ ቅስቀሳዎችንና የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን በማድረግ የልማት ተግባራትን መደገፍ
- ብሄር ተኮርና ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ ፎረሞችን በመጠቀም የታሪካዊ ግጭቶችንና ቅሬታዎችን ለመፍታት የውይይት መድረኮችን ማመቻቸት
- በተለያዩ አደረጃጀቶች/ርከኖች የሚገኙ የሰነ ጾታና ባህላዊ መዋቅሮችን ተጠቅሞ የስነልቦና ድጋፍ ስልጠናዎችንና ዲጋፎችን ማድረግ
- የግጭት አፈታት ማስገንዘቢያዎችንና ስልጠናዎችን ለአካባቢው ሽማግሌዎችና ለወጣት አመራሮች መስጠት ግጭቶችም ከፍተኛ ጉዳት ሳያደርሱ ለመፍታት መስራት
- በተለያዩ ባህሎች እንዲሁም በድምበር ተሻጋሪ ፎረሞች ውስጥ ታሪካዊ የቅሬታ መፍቻ የውይይት ሂደቶችን ማመቻቸት
- ሰፋፊና ወጣቱን ማዕከል ያደረጉ የማህበረሰብ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት፡፡ ውይይቶቹ የአቻ ለአቻ አቀራረቦችን ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ መድረኮችን /ፕሮግራሞችን/ በመጠቀም የህገወጥ ፍልሰት አደጋዎችንና ውጤቶችን ትኩረት ሰጥተው ሊከናዎኑ ይችላሉ
- ሕገወጥ ፍልሰትን በተመለከተ ለህገወጥ አዘዋዋሪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት የተጠያቂነት አሰራሮች እንድኖሩ ማገዝ
- በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የወጣቶች የሽማግሌዎች መዋቅሮችን ለምሳሌ የኮሙኒቲ ኬር ኮአሊሽን (ሲሲሲ) የመሳሰሉትን ማጠናከር፡ ለህገወጥ ስደት የሚዳርጉ ሁኔታዎችን ቅድመ መከላከል ላይ ትኩረት ሰጥተው እንድሰሩ ማስቻል ላይ መስራት

- ነባር ባህላዊ የሰላም መዋቅሮችን/አደረጃጀቶችን (ለምሳሌ የሽማግሌዎች ምክር ቤቶች) ወይም መደበኛ የሰላም ኮሚቴዎችን በዘመናዊ የሽምግልና ስልጠና ማጠናከር፡ በግጭት አፈታት ዙሪያ የማማከር አገዛ ማድርግ

### 4.1.5. *በሴቶች መብቶች እና አመራር ማጎልበት*

- ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ለደረሰባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ (ለምሳሌ ማማከር ፣ የነጻ ህግ አገለግሎት መስጠት)
- ጾታዊ ጥቃትን መከላከል ላይ ትኩረት ያደረጉ ዘርፈ ብዙ ቅስቀሳዎችን ማድረግ
- ለሴቶች የስነ አመራርና አድቮኬሲ ሰልጠናዎችን መስጠት፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የአመራርነት ቦታ አንድኖራቸው ማገዝ
- በገጠር አካባቢ ለሚኖሩ ሴቶች የአመራር ሰልጠና ድጋፍ መስጠት
- ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መከላከል ላይ መስራት
- ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጠቂዎች ድጋፍ ማቅረብ እና
- ሴቶች አነስተኛ ንግዶችን እንዲጀምሩ በማይክሮ ፋይናንስና የቴክኒክ ትምህርት የሙያ ስልጠና መስጠት፣ የሴቶች የራስ አገዝ ቡድኖችን ማቋቋም፣ በጎጂ ልማዶች፣ ጾታዊ ጥቃት፣ "ሚንጊ" እና ያለዕድሜ ጋብቻ ላይ ቅስቀሳዎችንና የማኅበረሰብ ውይይቶችን ማካሄድ እና የሴቶች ማህበራት በአካባቢ አስተዳደር እንዲሳተፉ መደገፍ።

### 4.1.6. *በመሰረታዊ አገልግሎቶች የማህበራዊ ተጠያቂነት ዘርፍ ዙሪያ*

- ዜጎች አገልግሎት በሚያገኙባቸው የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት(ትምህርት ቤት፣ ጤና ጣቢያ ወይም የውሃ አገልግሎት) የማህበራዊ ተጠያቂነት እንድሰፍን ከማድረግ አኳያ የማህበራዊ ተጠያቂነት መሳሪያዎችን ወይም ማህበራዊ ኦዲትን ሂደቶችን መተግበር፡ የተገኘውንም መረጃ በመጠቀም የአገለግሎት አሰጣጡን ፍትሃዊነት መከታተልና መቆጣጠር እንድችሉ ማብቃት
- ማህበረሰብ አገልግሎት ተኮር የሆኑ ኮሚቴዎችን ማቋቋም፡ ማሰልጠንና ሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች የሚገባቸውን አገልግሎት ከሚመለከታቸው አካላት እንዲያገኙ ማስቻልና አገልግሎት ሰጪዎች አስፈላጊውን አቅርቦት እንድሰጡ ከማድረግ አኳያ ክትትልና ቁጥጥር አንድኖር ማስቻል
- የውሃ ተጠቃሚዎች ኮሚቴዎችን ወይም የጤና ተቋም አስተዳደር ኮሚቴዎችን ማቋቋምና ማሰልጠን፣ በዚህም አካባቢያዊ አገልግሎቶችን ከመቆጣጠር ባሻገር ከወረዳ ደረጃ አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ለክትትልና ለጋራ ተጠቃሚነት የሚያገለግሉ መደበኛ የግንኙነት መዋቅሮች እንዲሆኑ ማጠናከር።

## 5. ባለ ፈርጀ ብዙ ጉዳዮች (Cross-cutting issues)

ባለ ፈርጀ ብዙ ጉዳዮች የሚባሉት በዚህ የፍላጎት መግለጫ በሁሉም ፕሮጀክቶች፣ ፕሮግራሞች እና ተግባራት ውስጥ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው አስፈላጊ ጭብጦች ናቸው። ይህ የፍላጎት መግለጫ (ኢ ኦ አይ) እንደ ፆታ እኩልነትና ማህበራዊ አካታችነት (ጀሲ)፣ ለግጭት አጽንኦት መስጠት (ኮንፍሊክት ሴንሲቲቪቲ)፣ የማህበረሰብ የባለቤትነት ስሜትና የፕሮጀክት ዘላቂነት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ትስስር እና ቅንጅት ግንባታ፣ የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ፣ የዴሞክራሲ መርሆዎች፣ መልካም አስተዳደር ተግባራት፣ የህጻናት መብቶች፣ እንዲሁም የሴቶች፣ የወጣቶች እና የአካል ጉዳተኞች መብቶችን ጨምሮ

የተገለሉ እና ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን መብቶችን በተገቢው ሁኔታ የሚያካትቱ ፕሮጀክቶችን ቅድሚያ የሚሰጥ ነው። በ ኢ ኦ አይ ግምገማ ሂደት ውስጥ እነዚህ ጉዳዮች ከፍተኛ ክብደት የሚሰጣቸው የማመልከቻው አካል ናቸው።

## 6. የፍላጎት መግለጫ ጥሪ ማሳወቂያዎች እና የመረጃ ክፍለ ጊዜዎች

ክርስቲያን ኤይድ እና አጋር ድርጅቶቹ የፍላጎት መግለጫ ((ኢ ኦ አይ)) ጥሪውን ግልጽነትን እና ለሁሉም አመልካቾች እኩል ዕድልን በሚያረጋግጥ መልኩ በስፋት ያስተዋውቃሉ/ያሰራጫሉ። ይህም በዋናነት በኢትዮጵያን ሪፖርተር፣ በኢትዮጅብስ፣ እንዲሁም እንደ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ባሉ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ስርጭቶች የሚለቀቁ ይሆናል። በተጨማሪም ጥሪው በተለያዩ አጋር ድርጅቶች ድረ-ገጾች ላይ ይታተማል፤ ከእነዚህም መካከል የአውሮፓ ህብረት፣ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ፎረም፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን፣ የክርስቲያን በጎ አድራጎትና ልማት ድርጅቶች ህብረት እና ሌሎችም ድረ-ገጾች ይገኙበታል። እንዲሁም በክልል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኔትወርኮች፣ የመንግስት ተቋማት እንደ ክልል ፋይናንስ ቢሮ፣ የፍትሕ ቢሮ፣ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ቢሮ የማስታወቂያ ቦታዎች ላይ በሚለጠፉ ፖስተሮች፣ እና በእነዚህ ተቋማት የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች አማካኝነት ይሰራጫል። እነዚህ ጥሪዎች እንደ አስፈላጊነቱ በእንግሊዝኛ፣ በአማርኛ፣ በትግርኛ እና በሌሎች ተገቢ ቋንቋዎች ይቀርባሉ። የፍላጎት መግለጫ (ኢ ኦ አይ) ጥሪው ለ**አንድ ወር** ያህል(**ከሰኔ 28 እስከ ሀምሌ 28 ቀን 2018 ዓም**) በአየር ላይ ይቆያል።

**በተጨማሪም** ስለ የማመልከቻ ሂደቱ፣ የመወዳደሪያ መስፈርቶች እና ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች ተጨማሪ ማብራሪያ ለመስጠት አጭር የመረጃ ክፍለ ጊዜ ከጥያቄና መልስ ፕሮግራም ጋር በበይነመረብ (ኦንላይን) በማይክሮሶፍት ቲምስ አማካኝነት ይዘጋጃል። ማንኛውም በፕሮግራሙ ለመሳተፍ ፍላጎት ያለው አካል መተግበሪያውን ማውረድ ሳይጠበቅበት በቀጥታ መሳተፍ ይችላል። የመረጃ እና የጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜው ከታች በተጠቀሰው ሊንክ አማካኝነት **ሀምሌ 10 ቀን 2018 ከሰዓት ከ8:00 እስከ 10:00** ድረስ ይካሄዳል።

**የስብሰባ ማስፈንጠሪያ/ሊንክ:** EU CSF+ EOI Call Drop In and Info Session | Meeting-Join | Microsoft Teams

የስብሰባ መለያ (Meeting ID): 373 742 650 663 708

የሚስጥር ኮድ (Passcode): j9ax6E5q

የመረጃ፡ የጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜውን ማጠቃለያ እና የተቀዳውን ቪዲዮ በድረ ገጹ ላይ በሚቀርቡ ሊንኮች አማካኝነት ይጋራል። ይህም በመረጃ ክፍለ ጊዜው መሳተፍ ያልቻሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የማመልከቻ ጥሪውን መስፈርቶችና ሂደቶች በሚገባ እንዲረዱ ያግዛል። በተጨማሪም፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የማመልከቻ ሊንኮችን ለማግኘት ወይም የማመልከቻ ሂደቱ ላይ ችግር ካጋጠማቸው፣ በየክልሉ ከተመደበው ተወካይ/ሃላፊ (ከታች በክፍል 7.4. በተጠቀሰው አድራሻ መሠረት) በስልክ ጥሪ አማካኝነት ማብራሪያ እና ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። ይህም ለሁሉም አመልካቾች ፍትሃዊ እና ተመጣጣኝ ተደራሽነት እንዲረጋገጥ ለማድረግ ያግዛል ተብሎ ይታሰባል።

## 7. ለፍላጎት ማመልከቻ ጥሪው የቀረቡ መስፈርቶች እና ደንቦች

### 7.1. ለፍላጎት መግለጫ ብቁ የሆኑ ድርጅቶች የምርጫ መስፈርቶች

| አካል | ትርጓሜ (Definition) | የብቁነት መስፈርቶች (Eligibility Criteria) | የግራንት አይነት |
|---|---|---|---|
| አነስተኛ ወይም ጀማሪ ደረጃ ላይ የሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች | **ምድብ አንድ**<br><br>አነስተኛ ወይም ጀማሪ አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ወይም ማህበረሰብን መሠረት ያደረጉ ድርጅቶች (ሲ. ቢ. ኦስ) ሲሆኑ፣ ውስን የተግባር መዋቅር ያላቸው፣ በሕጋዊ መንገድ የተቋቋሙ እና በአዲሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1113/2011) መሠረት በክልል ወይም በብሔራዊ ደረጃ እንደገና የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ መሆን አለባቸው።<br>እነዚህ ድርጅቶች በሚያመለክቱበት ክልል ውስጥ ተቀማጭነት ያላቸው እንዲሆኑ ይጠበቃል፤ ሆኖም ግን በሚያመለክቱበት ክልል ውስጥ የሥራ ልምድ እንዲኖራቸው አይጠበቅም (የፕሮጀክት ትግበራ ልምድ የግዴታ መስፈርት አይደለም) ።<br><br>በተጨማሪም፣ እነዚህ ድርጅቶች በቀጣይ ጊዜ የሚጠናከሩ ቢሆንም ቢያንስ መደበኛ ያልሆነ (ሰብ ስታንዳርዳይዝድ) ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊኖራቸው ይገባል፤የሥራ ዕቅድ ሊኖራቸው ይገባል፤ ቢያንስ ከ2 እስከ 3 የተመዘገቡ ቋሚ ሠራተኞች ወይም በጎ ፈቃደኞች ሊኖራቸው ይገባል፤ ከእነዚህ ውስጥ ቢያንስ አንዱ የፋይናንስ ወይም የሂሳብ ሠራተኛ መሆን ይኖርበታል።<br><br>በተጨማሪም የድርጅቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ከላይ የተጠቀሱትን የትኩረት ዘርፎች ማካተት ያለበት ሲሆን፣ ድርጅቱ በሴቶች፣ በወጣቶች ወይም በአካል ጉዳተኞች ላይ ትኩረት ያደረጉ ወይም በእነርሱ የሚመሩ መሆን አለባቸው።<br><br>***ማሳሰቢያ፡-*** ድርጅቶቹ ባመለከቱበት ክልል ውስጥ መኖራቸውን ለማረጋገጥ፣ ከሚመለከተው የክልል ፋይናንስ ቢሮ ጋር ግንኙነት ተደርጎ ማረጋገጫ ይወሰዳል። | አመልካች ድርጅቶች ለዚህ የአነስተኛ ድጋፍ (ስሞል/ማይክሮ ግራንት) ብቁ ለመሆን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡-<br>• ለዚህ ምድብ የተቀመጠው ትርጓሜ ውስጥ የተመለከቱትን ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።<br>• ለሁሉም አመልካቾች የተቀመጡትን ሁሉንም አጠቃላይ የብቁነት መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።<br>• የግራንት አስተዳደር ልምድ መኖሩ የግዴታ መስፈርት አይደለም።<br>• የፋይናንስ አስተዳደርና ሪፖርት ዝግጅትን ሊደግፍ የሚችል ቢያንስ አንድ የፋይናንስ/የሂሳብ ሠራተኛ ወይም የተመዘገበ በጎ ፈቃደኛ ሊኖራቸው ይገባል።<br>• ለአንድ ፕሮጀክት ከ10,000 ዩሮ ያልበለጠ (በኢትዮጵያ ብር ተመጣጣኝ ዋጋ) ግራንት መቀበል የሚችሉ መሆን አለባቸው። ግራንቱን እስከ ሶስት ዙር በሚደርስ ክፍያዎች (ኢንስቶልመንት) ለመቀበል ዝግጁ መሆን አለባቸው። | የአነስተኛ ግራንት (ስሞል/ ማይክሮ ግራንት) |
| | **ምድብ ሁለት**<br><br>አነስተኛ አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ወይም ማህበረሰብ መሠረት ያደረጉ ድርጅቶች | አመልካች ድርጅቶች ለዚህ ምድብ ብቁ ለመሆን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡- | አነስተኛ / ማይክሮ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | (ሲቢኦስ) ሲሆኑ፣ ውስን የተግባር መዋቅር ያላቸው፣ በሕጋዊ መንገድ የተቋቋሙ እና በአዲሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1113/2011) መሠረት በክልል ወይም በብሔራዊ ደረጃ እንደገና የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ መሆን አለባቸው። <br><br> እነዚህ ድርጅቶች በሚያመለክቱበት ክልል ባለፉት 3 ዓመታት ውስጥ ሲሰሩ የቆዩ መሆን አለባቸው፤ ቢያንስ የተልዕኮ ማስፈጸሚያ (ኦፕሬሽናል) ዕቅድ እና የአስተዳደር (ገቨርናንስ) ፖሊሲዎች ሊኖሯቸው ይገባል። በተጨማሪም ከ3 እስከ 5 ቋሚ ሠራተኞች ሊኖሯቸው ይገባል፣ ወይም በተመዘገቡ የበጎ ፈቃድ አባላት አማካኝነት ሲሠሩ የቆዩ መሆን አለባቸው። ባለፉት ሶስት ዓመታት ውስጥ ያላቸው ዓመታዊ ገቢ በኢትዮጵያ ብር ከተጠየቀው የፕሮጀክት በጀት መጠን ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት። በወረዳ ወይም በክልል ደረጃ የሚሠሩ፣ ውስን የጂኦግራፊያዊ ሽፋን ያላቸው መሆን አለባቸው። በተጠቀሱት የትኩረት ዘርፎች ተግባራዊ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል። በሴቶች፣ በወጣቶች ወይም በአካል ጉዳተኞች ላይ ትኩረት ያደረጉ ወይም በእነርሱ የሚመሩ ድርጅቶች መሆን አለባቸው። <br><br> **ማሳሰቢያ፡-** ድርጅቶቹ ባመለከቱበት ክልል ውስጥ የሚሰሩ መሆናቸውን እና በአመልካቾች የተገለጸውን አመታዊ የበጀት መጠን ለማረጋገጥ፣ ከሚመለከተው የክልል ፋይናንስ ቢሮ ጋር ግንኙነት ተደርጎ ማረጋገጫ ይወሰዳል። አመልካቾች ለባለፉት **ሶስት ዓመታት (2023 – 2025 እ.አ.አ)** የድርጅታቸውን ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርቶች እንዲያቀርቡ ይመከራሉ። | • ለዚህ ምድብ የተቀመጠው ትርጓሜ ውስጥ የተመለከቱትን ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው። <br><br> • ለሁሉም አመልካቾች የተቀመጡትን አጠቃላይ የብቁነት መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው። <br><br> • ባለፉት **ሶስት ዓመታት (2023–2025 እኤአ)** ውስጥ ለተጠየቀው የግራንት መጠን (በኢትዮጵያ ብር ተመጣጣኝ ዋጋ) የሚተካከል ቢያንስ **አንድ ግራንት በማስተዳደር የተረጋገጠ ልምድ** ሊኖራቸው ይገባል። <br> • የፋይናንስ ሪፖርት ዝግጅትና አስተዳደርን ሊደግፍ የሚችል ቢያንስ **አንድ የፋይናንስ/የሂሳብ ባለሙያ ሠራተኛ** ሊኖራቸው ይገባል። ይህ መረጃ የማመልከቻው አካል ሆኖ በማረጋገጫው (ድክላሬሽኑ) መቀመጥአለበት። | ግራንት (Small/ Micro Grant) |
| መካከለኛ /ትልልቅ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች | እነዚህ በተጠቀሱት ክልሎች ውስጥ የሚሰሩ መካከለኛ አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሲሆኑ፣ በሕጋዊ መንገድ የተቋቋሙ እና በአዲሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1113/2011) መሠረት በክልል ወይም በብሔራዊ ደረጃ እንደገና የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ መሆን አለባቸው። <br><br> እነዚህ ድርጅቶች በሲቪል ማህበራት ዘርፍ ከ5 ዓመት በላይ የሥራ ልምድ ያላቸው መሆን አለባቸው። የተሟሉ የአስተዳደር እና የሕግ ተገዢነት (ኮምፕሊያንስ) ፖሊሲዎች ሊኖሯቸው ይገባል። ከ3 | • ለዚህ ምድብ የተቀመጠው ትርጓሜ ውስጥ የተመለከቱትን ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው። <br><br> • ለሁሉም አመልካቾች የተቀመጡትን አጠቃላይ የብቁነት መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው። <br><br> • ባለፉት 3 ዓመታት ውስጥ ለተጠየቀው የግራንት መጠን (በኢትዮጵያ ብር ተመጣጣኝ | የሜሶ ግራንት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ዓመት በላይ የሚሸፍን ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊኖራቸው ይገባል። የተጠናከረ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት እና አሠራር ሊኖራቸው ይገባል። ቢያንስ ከ3 በላይ የቴክኒክና የድጋፍ ሠራተኞችን ያካተተ ቋሚ የሰው ኃይል ሊኖራቸው ይገባል። በተቋማዊ አቅም የተጠናከሩ እና የተደራጁ መሆን አለባቸው። ዓመታዊ ወጪያቸው ከተጠየቀው የግራንት መጠንና (በኢትዮጵያ ብር ተመጣጣኝ ዋጋ) ከፍ ያለ መሆን አለበት። አመልካቾች የድርጅቱን የፋይናንስ ደረጃ የሚያሳዩ የመጨረሻ ሶስት ዓመታት (2023–2025 እ.አ.አ) የዓመታዊ ኦዲት ሪፖርቶች ማቅረብ የጠበቅባቸዋል። ድርጅቱ በርካታ ፕሮጀክቶች እያስተዳደረ እያለ፣ የአንድ ፕሮጀክት ኦዲት ሪፖርት ብቻ ማቅረብ ማመልከቻው ውድቅ እና ከውድድር ውጪ (በላክሊስት) መሆንን ሊያስከትል ይችላል።<br><br>እነዚህ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶቹ በኢዩ ሲኤስኤፍ ፕሮግራም በተለዩት የትኩረት ዘርፎች ውስጥ የሥራ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል። በተጨማሪም ድርጅቶቹ በሴቶች፣ በወጣቶች ወይም በአካል ጉዳተኞች ላይ ትኩረት ያደረጉ ወይም በእነርሱ የሚመሩ ድርጅቶች መሆን አለባቸው።<br><br>**ገደቦች፦** በሶስት ዓመታት **<u>አማካይ</u>** ከ 100,000 ዩሮ (ከ18,300,000 ብር በላይ) **በላይ** በጀት ያስተዳደሩ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች "አነስተኛ" ወይም "አነስተኛ ተቋማዊ አቅም ያላቸው" ተብለው ስለማይቆጠሩ ለዚህ የድጋፍ ፕሮግራም ብቁ አይሆኑም።<br><br>**ማሳሰቢያ፦** አመልካቾች የገለጹትን የበጀት መጠን ለማረጋገጥ ከሚመለከተው የክልል ፋይናንስ ቢሮ ጋር በመገናኘት ማረጋገጫ ይወሰዳል። | ዋጋ) የሚበልጥ ግራንት በማስተዳደር የተረጋገጠ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል።<br><br>• ከተገለሉ እና ተጋላጭ የማህበረሰብ ቡድኖች ጋር በመሥራት እና ከላይ በክፍል 4.1 ከተለዩት ተመሳሳይ የትኩረት ዘርፎች ውስጥ ከ5 ዓመት በላይ ተግባራዊ የሥራ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል።<br><br>• ድርጅቱ በሴቶች፣ በወጣቶች ወይም በአካል ጉዳተኞች ጉዳይ ላይ ትኩረት ያደረገ ወይም በእነዚህ ቡድኖች የሚመራ መሆን አለበት። | |
| ማህበር (አሶሴሽን) | **ማህበር** ማለት፣ ቁጥራቸው አምስት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አባላት የሚቋቋም እና ጠቅላላ ጉባዔው የበላይ ውሳኔ ሰጪ አካል የሆነበት ድርጅት፣ በሕጋዊ መንገድ የተቋቋሙ እና በአዲሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1113/2011) ወይም በሌላ ሕጋዊ ድንጋጌ መሠረት በክልል ወይም በብሔራዊ ደረጃ እንደገና የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ መሆን አለባቸው።<br><br>ይህ ማህበር በሲቪል ማህበራት ዘርፍ ከ5 ዓመታት በላይ የሥራ ልምድ ያለው መሆን አለበት። ከተጠየቀው | • ለዚህ ምድብ የተቀመጠው ትርጓሜ (Definition) ውስጥ የተመለከቱትን ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።<br><br>• ለሁሉም አመልካቾች የተቀመጡትን አጠቃላይ የብቁነት መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው። | የሜሶ ግራንት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የግራንት መጠን (በኢትዮጵያ ብር ተመጣጣኝ ዋጋ) በላይ የሆነ በጀት በማስተዳደር የፈንድ አስተዳደር ልምድ ሊኖረው ይገባል። ለሶስት ዓመታት የሚሆን ወይም የተመሳሳይ ጊዜ ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊኖረው ይገባል። የአስተዳደር እና የሕግ ተገዢነት (ኮምፕሊያንስ) ፖሊሲዎች ሊኖሩት ይገባል። የተደራጀ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓትና አሠራር ሊኖረው ይገባል። ቢያንስ 5 የቴክኒክና የድጋፍ ሰራተኞች ሊኖሩት ይገባል፣ ወይም ከተመዘገቡ የበጎ ፈቃድ አባላት ጋር ሲሰራ የቆየ መሆን አለበት። ዓመታዊ ወጪው ከተጠየቀው የግራንት መጠን (በኢትዮጵያ ብር ተመጣጣኝ ዋጋ) በላይ መሆን አለበት።<br><br>የብቁነት ገደቦች በሶስት ዓመታት (2023–2025 **እ.አ.አ**) አማካይ ከ100,000 ዩሮ (18,300,000 ብር) በላይ በጀት ያስተዳደሩ ማህበራት "አነስተኛ" ወይም "ያልተጠናከሩ" ተቋማት ተብለው አይቆጠሩም፤ ስለዚህ ለዚህ ግራንት ፕሮግራም ብቁ አይሆኑም።<br><br>አመልካቾች የ2023፣ 2024 እና 2025 **እ.ኤ.አ** ዓመታዊ የድርጅት ኦዲት ሪፖርቶችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል። አመልካች ማህበሩ ከአንድ በላይ ፕሮጀክቶችን በማስተዳደር ላይ እያለ፣ የአንድ ፕሮጀክት ኦዲት ሪፖርት ብቻ ካቀረበ ከውድድሩ ይሰረዛል። በተጨማሪም ብላክ ሊስት ውስጥ እንድገባ ይደረጋል።<br><br>ማህበሩ በኢዩ ሲ ኤስ ኤፍ ፕሮግራም በተለዩት የትኩረት ዘርፎች ውስጥ የሥራ ልምድ ሊኖረው ይገባል፤ በተጨማሪም በሴቶች፣ በወጣቶች ወይም በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ ላይ ትኩረት ያደረገ ወይም በእነርሱ የሚመራ መሆን አለበት።<br><br>**ማሳሰቢያ፡-** አመልካቾች የገለጹትን የበጀት መጠን ለማረጋገጥ ከሚመለከተው የክልል ፋይናንስ ቢሮ ጋር መገናኘት እና ማረጋገጫ ይወሰዳል።<br><br>ከመንግስት ጋር ያልተቆራኙ (non-government affiliated) የሙያ ወይም ማህበራዊ ማህበራት ለምሳሌ የመምህራን ማህበር፣ የሴቶች ማህበር፣ የቤት ሰራተኞች ማህበር፣ የወጣቶች ማህበር፣ የጡረተኞች ማህበር፣ የአካል ጉዳተኞች ማህበር፣ የህዳጣን ማህበረሰብ ቡድኖች መብት ማህበራት ወዘተ ያካትታል። | • ባለፉት 3 ዓመታት ውስጥ ለተጠየቀው የግራንት መጠን (በኢትዮጵያ ብር ተመጣጣኝ ዋጋ) የሚበልጥ ግራንት በማስተዳደር የተረጋገጠ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል።<br><br>• በተገለሉ እና ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር በመሥራት እና ከላይ በክፍል 4.1 በኢዩ ሲ ኤስ ኤፍ ፕሮግራም የተለዩት የትኩረት ዘርፎች ውስጥ ከ3 ዓመት በላይ ተግባራዊ የሥራ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል። እንዲሁም በሴቶች፣ በወጣቶች ወይም በአካል ጉዳተኞች ጉዳይ ላይ ትኩረት ያደረገ ወይም በእነዚህ ቡድኖች የሚመራ መሆን አለበት። | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| በመነሻ ደረጃ ላይ የሚገኙ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ትስስሮች (ኔትወርኮች) | በሕጋዊ መንገድ የተመዘገቡ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ቡድኖች (ቢያንስ 10 እስከ 50 የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አባላት ያሉባቸው)፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ፎረሞች፣ ቅንጅቶች፣ ፌዴሬሽኖች፣ ኮንሶርቲየሞች ወይም ኔትወርኮች፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ በሕጋዊ መንገድ የተቋቋሙ እና በአዲሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1113/2011) ወይም በሌላ ሕጋዊ ድንጋጌ መሠረት በክልል ወይም በሀገር አቀፍ ደረጃ እንደገና የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ መሆን አለባቸው። በዚህ ዘርፍ ቢያንስ ለ5 ዓመታት የሠሩ እና አሁንም በመስራት ላይ የሚገኙ መሆን አለባቸው።<br><br>እንዲሁም፣ የተደራጀ የአስተዳደር እና የሕግ ተገዢነት (ኮምፕሊያንስ) ፖሊሲዎች ያሏቸው፣ ከ3 እስከ 5 ዓመት የሚሸፍን ስትራቴጂክ ዕቅድ ያዘጋጁ፣ የተደራጀ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ያላቸው፣ ከ3 በላይ ቋሚ ሠራተኞች (ቴክኒካልና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች) ያሏቸው፣ የፕሮጀክት አስተዳደር ሥርዓት ያላቸው እና ዓመታዊ ወጪያቸው/ገቢያቸው ከሚጠየቀው የገንዘብ መጠን የሚበልጥ (በኢትዮጵያ ብር ተመጣጣኝ መጠን) መሆን አለበት።<br><br>**ማሳሰቢያ፡-** አመልካቾች ያሳወቁትን የበጀት መጠን ለማረጋገጥ ከየክልሉ የፋይናንስ ቢሮዎች ወይም ሌላ የሚመለከተው አካል ማረጋገጫ ይወሰዳል።<br><br>እነዚህ መሠረታዊ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኔትወርኮች በጋራ አጀንዳዎች እና/ወይም ጉዳዮች ላይ የሚሠሩ ሲሆን፣ ትምህርት ልውውጥን፣ ምክክርን፣ ትብብርን፣ ቅንጅትን፣ የአድቮኬሲ ሥራዎችን፣ የፖሊሲ ተፅዕኖ ፈጠራን፣ እንዲሁም የአቅም ግንባታንና ምቹ የሥራ አካባቢ ሁኔታን ለማጠናከር/ ለማሳለጥ ያለሙ ናቸው። ዓላማቸውም በአንድ ወይም በብዙ ዘርፎች ውስጥ ያሉ ዕድሎችን፣ ተግዳሮቶችን እና ስትራቴጂዎችን በጋራ በመለየት የሲቪል ማኅበረሰብን ምህዳርን ለመለወጥ ነው።<br><br>**ማስታወሻ:** የአካባቢ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ኔትወርኮች ስትራቴጂካዊ አጋሮች ተደርገው ስለሚታዩ፣ የጥሪውን መስፈርቶች እስካሟሉ ድረስ ለዚህ ግራንት እንዲያመለክቱ በጣም ይበረታታሉ። | • በትርጉሙ ውስጥ የተጠቀሱትን ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል።<br><br>• ለሁሉም አመልካቾች የተቀመጡትን አጠቃላይ የብቁነት መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።<br><br>• በ2023–2025 እ.አ.አ ባሉት የመጨረሻ 3 ዓመታት ውስጥ ከሚጠየቀው የድጋፍ ገንዘብ መጠን (በኢትዮጵያ ብር ተመጣጣኝ ዋጋ) የሚበልጥ ግራንት በማስተዳደር የተረጋገጠ ልምድ ሊኖረው ይገባል።<br><br>• በተገለሉ እና ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር በመስራት እና በኢ ዩ ሲ ኤስ ኤፍ ፕላስ ፕሮግራም በተለዩ የትኩረት ዘርፎች ዙሪያ ቢያንስ የ3 ዓመት ተግባራዊ ልምድ ሊኖረው ይገባል። ይህም በተለይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በቅንጅት፣ በትምህርትና ልምድ ልውውጥ፣ በኔትወርኪንግ፣ በአድቮኬሲ እና በፖሊሲ ተፅዕኖ ፈጠራ (Policy Influencing) ዘርፎች የአቅም ማጠናከርን ያካትታል። | የሜሶ ግራንት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ከዚህ በፊት ልምድ የሌላቸው አዲስ መሠረታዊ ኔትወርኮችም ሁሉንም መስፈርቶች ካሟሉ በማይክሮ ምድብ I (አንድ) ማመልከት ይችላሉ። ኔትወርኮች ያመለከቷቸውን ፕሮጀክቶች በቀጥታ ለማስተዳደርና ለመፈጸም ሙሉና ቀጥተኛ ኃላፊነት ይወስዳሉ፤ እንደ መካከለኛ አካል (Intermediary) ሆኖ የተጠየቀውን ግራንት ለሌላ ሦስተኛ ወገን መስጠት አይቻልም። | | |

***ማስታወሻ፡***

አነስተኛ/ማይክሮ ግራንት ምድብ አንድ አመልካቾች እስከ 10,000 ዩሮ ድረስ ግራንት ለማግኘት ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡ አነስተኛ/ማይክሮ ግራንት ምድብ ሁለት አመልካቾች ከ15,000 እስከ 30,000 ዩሮ ግራንት ለማግኘት ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም የሜሶ አመልካቾች ከ30,000 እስከ 50,000 ዩሮ ክልል ውስጥ ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡

### 7.2. አመልካቾች ሊያሞሉ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች /መስፈርቶች/

የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች በሁሉም የግራንት አስተዳደር ሂደት ደረጃዎች ላይ ባሉ አመልካቾች ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናሉ፡

- ✓ በክፍል 7.1. ላይ የተመለከቱትን የብቁነት መስፈርቶችን በሙሉ በሙሉ የሚያሟሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች
- ✓ የፍላጎት ማመልከቻ ካስገቡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አስፈላጊውን ውጤት(EOI assessment result) ያስመዘገቡ አመልካቾች
- ✓ እያንዳንዱ ድርጅት በአንድ የጂኦግራፊ ክልል/ከተማ አስተዳደር ውስጥ ብቻ የግራንት ማመልከቻውን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ አንድ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ከአንድ በላይ ክልል/ከተማ አስተዳደር ያቀረበ ከሆነ መስፈርቱን እንዳላሟላ ተቆጥሮ ከወድድር ውጪ ይሆናል
- ✓ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በኃላ የሚቀርቡ ማንኛውም የግራንት ማመልከቻዎች ፣ እንዲሁም አስፈላጊ ሰነዶች ያልተሟሉበት እና የማመልከቻ ቅጹን ያልጠበቀ ማመልከቻ ውድቅ የሚደረግ ይሆናል
- ✓ ሁሉም ማመልከቻዎች ሊዘጋጁ እና ሊቀርቡ የሚገባቸው በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቻ ይሆናል
- ✓ አመልካቾች ለግራንት ውድድር እና የፍላጎት መግለጫ ለማዘጋጀት/ለማቅረብ ያወጧቸው ወጪዎች በአመልካችቾች ብቻ የሚሸፈኑ ይሆናሉ፡፡
- ✓ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በሚከተሉት ምክንያቶች ውድቅ ይሆናሉ፡፡
    - ○ የውድድር መስፈርቶችን ጥራት ወይም ፍላጎቶች ያላሟላ ከሆነ
    - ○ በድርጅታዊ የአቅም ዳሰሳ ወቅት (ዲዲኤ) የሚገጥሙ ወሳኝ ግኝቶች
    - ○ በፕሮግራሙ ህያውነት/ቀጣይነት/ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ያልተጠበቁ ሁኔታዎች
- ✓ የ ኢዩ ሲኤስ.ፍ. ፕላስ ፕሮግራም የፕሮጀክት ፍላጎት መግለጫውን ይዘት፣ አሰራር ወይም በጀት በተመለከተ ከሚመለከታቸው አመልካቾች ጋር ተፈላጊውን ውይይትና ድርድር የማድርግ መብት አለው፡፡ ይህም ከፍላጎት መግለጫው/ማመልከቻው በኋላ የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ፕሮግራሙ በግራንት አመልካቾች የተጠየቀውን ገንዘብ

በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሰርዝ  መብት አለው

- ✓ በዚህ የፍላጎት መግለጫ ላይ የተመለከቱት የፕሮጀክት አላማዎች እና ይዘቶች በፕሮፖዛል ማመልከቻው ላይ ሊቀየሩ አይችሉም
- ✓ ከዚህ ግራንት ፍላጎት መግለጫ መመሪያ ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሙ ማንኛውም አይነት ስህተት ወይም ከፍተኛ ክፍተት/ልዩነት በሚያጋጥምበት ጊዜ ማመልከቻው ውድቅ ይሆናል
- ✓ በእጅ የተጻፉ ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም
- ✓ በማንኛውም አይነት ሁኔታ ላይ የሚታይ የጽሁፍ ድግግሞሽ /ኩረጃ (plagiarism) ተግባር ከዚህ ውደድር ውድቅ የሚያስደርግ ይሆናል
- ✓ የፕሮጀክት በጀት ዕቅዱ በኢትዮጵያ ገንዘብ ወይም በብር መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ለማነጻጸሪያ ይረዳ ዘንድ ተመጣጣኝ የሆነው ገንዘብ ድምር በዩሮ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ አመልካቾች የበጀት እቅዱን በሚያዘጋጁበት ወቅት የአንድ ዩሮ ዋጋ በ183 ብር  ምንዛሬ ተመን መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡
- ✓ በኢዩ. ሲ.ኤስ.ፍ. ፕላስ ፕሮግራም ፕሮጀክት የመጀመሪያው ዙር ተሳትፈው የፕሮጀት ግራንት ያገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ደርጅቶቸ በዚህ ዙር ግራንት መሳተፍ አይችሉም፡፡
- ✓ አመልካቾች ከ 2015-2017 ዓ ም (2023_2025 እ.ኤ.አ.) አመታዊ የድርጅት ኦዲት ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡ ፡ አመታዊ የድርጅት አድት ሪፖርት ያላቀረቡ ድርጅቶች ከውድድር ወጭ ይሆናሉ፡፡ ጀማሪ ማይክሮ ደረጃ አንድ ድርጅቶች ይህንን ረፖርት ማቅረብ አይጠበቅባቸውም፡፡

## 7.3. የሚፈቀዱና የማይፈቀዱ ተግባራትና ወጪዎችነ በሚመለከት፡

### 7.3.1. የሚፈቀዱና የማይፈቀዱ ተግባራት

በዚህ ፕሮጀክት የሚፈቀዱና ፋይናንስ የሚደረጉ ተግባራት የሚባሉት ከፕሮጀክቱ አላማዎችና የትኩረት አቅጣጫዎች ጋር የቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ተግባራት ብቻ ናቸው፡፡ ሁሉም የሚታቀዱ ተግባራት ልዩና የሚለካ ውጤትን በተጨማሪም የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ሊቀርፉ በሚችሉበት መልኩ በብቃት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ ሊከናወኑ የታሰቡ ተግባራት ለዚህ የፍላጎት መግለጫ በተለይም ደግሞ ከኢዩ. ሲ.ኤስ.ፍ. ፕላስ ፕሮጀክት አላማዎችና የትኩረት አቅጣጫዎች ጋር በቀጥታ ያላቸውን ግንኙነት በሚገባ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህ የሚፈቀዱ ዝርዝር ተግባራት በሚከተሉት መልኩ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

i. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ሚና በመንግስት ፖሊሲዎች እና እቅዶች ክትትል ዙሪያ ማሳደግ

ii. በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መካከል የአጋርነት ግንባታን ማመቻቸት

iii. ዜጎችን በተለይም ወጣቶችን፣ ሴቶችን እንዲሁም አካል ጉዳተኞችን በዋናዋና ተግዳሮቶች ዙሪያ መቀስቀስ፡ ግንዛቤያቸውን ማሳደግና የውሳኔ ሰጪ አካላትን ተጠያቂ ማድረግ

iv. የተለያዩ የሚዲያ ፕላትፎርሞችን በመጠቀም በዋናዋና የፖሊሲ ጉዳዮች ዙሪያ የኢዩ. ሲ.ኤስ.ፍ. ፕላስ ፕሮጀክት የተግባቦትና የተቋም ግልጸኝነት ቢጋርን መነሻ በማድረግ መፈጸም

v. ትብብራዊ ጥናታዊ ሪፖርቶችንና  እና የፖሊሲ ሰነዶችን በማቅርብ በማስረጃ የተደገፉ የተጠየቃዊ ቅስቀሳ/ዘመቻ/ አንድኖር ማስቻል

vi. በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ውስጥ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅች አጋርነት ግንባታና የሲቪል ማህበረሰብ ትስስሮችን የሚፈጥሩ እንቅስቃሴዎች፤ እንዲሁም በድርጅቶች መካከል የአቅም ግንባታ ልውውጥ /ሽግግርን/ የሚደግፉ ተግባራት

vii. ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ፣ዜጎችን፣በተለይም ወጣቶችን ፣ሴቶችን ፣ አካል ጉዳተኞችን ለዲሞክራሲ ተሀድሶዎች እንዲንቀሳቀሱ የሚያደርጉ እንዲሁም ተጠያቂነትን ፣የህግ የበላይነትንና እኩልነትን የሚያጠናክሩ ዲሞክራሲያዊ ማሻሻያዎችን እንዲደግፉ የሚያደርጉ እንቅስቃሴዎች

viii. አነስተኛና በማደግ ላይ ያሉ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ሥራ በስልጠና፣ በማማከር፣ በድጋፍና በአእድቮኬሲ ላይ የሚያተኩሩ እንቅስቃሴዎች።

ix. በስርአተ ጾታ፣ ሰብአዊ መብቶች፣ የግጭት አትኩሮት፣ አካል ጉዳት እና ሌሎች ወሳኝ ጉዳዮች ላይ የሚያውጠነጥኑ እንቅስቃሴዎች

x. በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት፣ የሰብአዊ መብቶች፣ የግጭት ተጎጅነት፣ በአካል ጉዳትና ሌሎች ወሳኝ ዘርፎች (Cross-cutting) ውስጥ የሚያካተቱ ተግባራት

xi. ተጎጂ ለሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች የሰብአዊ መብት መደገፍ ላይ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በተለይም ለህጻናት፣ ወጣቶች እንዲሁም አካል ጉዳተኞች ልዩ አትኩሮት በመስጠት

**የማይፈቀዱ ተግባሮች/ስራዎች**

i. በአገሪቱ ሕግ የተከለከሉ ስራዎች

ii. በቀጥታ ከፖለቲካዊ ወይም ከሃይማኖታዊ አጀንዳዎች ጋር የተያያዙ ወይም የሚደግፉ እንቅስቃሴዎች

7.3.2. የሚፈቀዱና የማይፈቀዱ ወጪዎች

በኢዩ ሲኤስ ኤፍ ሥር በሰብግራንቲስ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን ለማስተዳደርና ለማስፈጸም አስፈላጊና ምክንያታዊ የሆኑ በበጀት የተያዙ አቅዶች የሚፈቀዱ ወጪዎች ይሆናሉ።

## የሚፈቀዱ ወጪዎች

- የህትመት፣ የፎቶ ኮፒ እና የህትመት ስርጭት ወጪዎች፤
- የመጓጓዣ ወጪዎች፤
- የሠራተኞች ደመወዝና ተያያዥ ወጪዎች፤
- ለፕሮጀክቱ ጥቅም ላይ ለሚውሉ በግል ወይም በመንግሥት ባለቤትነት የሚገኙ ሕንፃዎች የኪራይ ወጪ፣ ሆኖም ጠቅላላ የኪራይ ወጪው በተመሳሳይ አካባቢ ካሉ የግል ሕንፃዎች ከሚከፈለው የኪራይ መጠን ሙብለጥ የለበትም በተጨማሪም በተጠቃሚው ድርጅት ባለቤትነት ሥር ያለ ንብረት የኪራይ ወጪ ሊጠየቅ አይችልም።
- የኮንፈረንስና ወርክሾፕ ወጪዎች፣ ይህም የስብሰባ ዝግጅት፣ የአዳራሽ ኪራይ፣ ፖስታ፣ የስልክ ወጪዎች፣ እንዲሁም ለአሰልጣኞች፣ ለአቅራቢዎችና ለተሳታፊዎች የትራንስፖርትና የምግብ ወጪዎችን ሊያካትት ይችላል።
- የቢሮና እና ፕሮግራም አቅርቦት

- የፖስታ ወጪዎች
- ልዩ ክህሎቶች ወይም ልምዶች አስፈላጊ በሚሆኑበት ጊዜ ከማማከር አገልግሎት ጋር የተያያዙ ወጪዎች፤ እነዚህም ያለክፍያ የማይገኙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አግባብነት ያላቸው የድርጅቱ የግዢ ሂደቶች የአውሮፓ ህብረትን የተጠቃሚዎች የግዢ ህጎች በመከተል ሊተገበሩ ይገባል፡፡
- ከፕሮጀክት ጋር የተያያዙ የግንኙነት ወጪዎች
- የተሽከርካሪ እና መሳሪያ ክራይ
- የደህንነት ወጪዎች

**የማይፈቀዱ ወጪዎች:**

- የአልኮል መጠጦች
- ስጦታዎች ወይም ጉቦ ወይም እጅ መንሻዎች
- ለወታደራዊ አገልግሎት የሚወሉ ወጪዎች
- መኪና፣ ንብረት ወይም መሬት ግዥ
- ትልልቅ የካፒታል ወጪዎች
- ለመንግሥት ሠራተኞች የሚከፈሉ የማካካሻ ክፍያዎች
- የብሄራዊ አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች ደመወዝ
- ከፕሮጀክቱ የትግበራ ጊዜ ውጭ የተፈጸሙ ወጪዎች
- የእዳ መልሶ ክፍያ ፣ ከተያያዥ ወገኖች ዘንድ ያሉ በአግባቡ ያልተከፈሉ ክፍያዎች ወይም የወለድ ክፍያዎች ወይም የፋይናንስ ሊዝ/ኪራይ ጋር የተያየዙ የአገልግሎት ክፈያዎች
- ሙሉ በሙሉ ሃይማኖታዊ ወይም ፖለቲካዊ ይዘት ላላቸው ተግባራት የሚፈጸሙ ክፍያዎች
- ከሌሎች ምንጮች ፋይናንስ ለተደረጉ ሥራዎች ወይም እንቅስቃሴዎች የሚፈጸሙ ክፍያዎች
- በባንኮች ወይም በሌሎች የፋይናንስ ተቋማት የሚጣሉ አሉታዊ የወለድ መጠኖች
- በግራንት ኮንትራቱ ውስጥ የተከለከሉ ሌሎች ወጪዎች
- በሁሉም ደረጃ ለሠራተኞች የሚሰጡ ቦነሶች
- ከምንዛሬ ልውውጥ የሚከሰቱ ኪሳራዎች
- የገንዘብ መቀጮዎችና ሕጋዊ ወይም ወንጀል ቅጣቶች
- ሊከሰቱ የሚችሉ ኪሳራዎች ወይም ዕዳዎች የሚደረጉ ተቀማጭ ወጪዎች

ከዚህ በላይ የተቀመጡት የማይፈቀዱ ዝርዝሮች ሁሉ አቀፍ የሆኑ ዝርዝሮች አይደሉም፡፡ ክርስትያን ኤድ እና የፕሮጀክቱ ጥምር አባላት ቁልፍ የግራንት አጋሮች በመሆን በማመልከቻ ግምገማ ሂደት ላይ ሁሉንም ወጪዎች ሊገመግሙ እና ከሲ.ኤስ.ኤፍ ፕላስ መርሆች ውጪ የሆኑ ማናቸውም ወጪዎች ሊከለክሉ ይችላሉ፡፡

7.3.3. አመልካቾች ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች

ፕሮጀክቱ በዋነኛነት አነስተኛ ሀገር በቀልና በማደግ ላይ ያሉ የሲቪል ማህበረሰብ ደርጅቶች፣ ቅንጅቶች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ትስስሮች(ኔትዎርኮች)ና ማህበራትን ለመደገፍ እየሰራ ይገኛል፡፡ የሲቪል ማህበራት የፍላጎት ማቅረቢያ ማመልከት የሚችሉት ከፋይናንስ ሥራ አመራር ጋር የተያያዙ ስጋቶችን በአግባቡ መምራት የሚያስችላቸው አሰራርና ድርጅታዊ ብቃት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ አመልካቾች የሚከተሉትን ዝርዝር መስፈርቶች ሊያሟሉ ይገባል፡፡

- ✓ በኢትዮጵያ በፌደራል ወይም በክልል ደረጃ የተመዘገቡና አግባብነት ያለው የታደሰ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያላቸው
- ✓ አመልካቾች ፕሮጀክቱ በሚካሔድባቸው አካባቢዎች (በአዲስ አበባ ከተማ ፣በማእከላዊ ኢትዮጵያ ፣ ትግራይ ወይም ደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች) ዋና መስሪያ ቤት ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም የመስክ ጽ/ቤትና በጽ/ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ሊኖራቸው ይገባል

- ✓ ከገንዘብ ጋር በተያያዘ መልካም ካልሆኑ ልምምዶች ወይም ዕዳ ነፃ የሆኑ
- ✓ በሙስና፣ ማጭበርበር፣ ያታዊ ትንኮሳ እንዲሁም መልካም ባልሆኑ ድርጊቶች ጋር በተያያዘ ሪከርድ የሌለበት ወይም በክስ ሒደት ውስጥ የማይገኙ
- ✓ አግባብነት ያለው ውስጣዊ የቁጥጥር ስርአት (የፋይናንስ አሰራር፣ የግዢ ሂደት ፣ የሰው ሀብት አመራር፣ የፕሮጀክት አስተዳደር፣ ወዘተ) ያላቸው ወይም እንዲኖራቸው ቁርጠኝነት ያላቸው
- ✓ የፋይናንስ ሥርዓቱን መደገፍ የሚችል ቢያንስ አንድ የፋይናንስ/የሂሳብ ሰራተኛ ያላቸው
- ✓ አመልካች ድርጅቶች ወይም በድርጅቱ ውስጥ የሚሠሩ ግለሰቦች በአውሮፓ ህብረት በተጣለ የገደብ እርምጃ ዝርዝር ውስጥ ያልተከተቱ
- ✓ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ባለሥልጣን በአዋጅ ያወጣውን የ20/80 (20 በመቶ የአስተዳደራዊ ወጭ እና 80 በመቶ የፕሮግራም ወጪ) በሚገባ የሚያሟሉ
- ✓ አስገዳጅ የሆኑ የሥራ ሥርዓቶችን (የተጋላጭ ሰዎች ከለላ ፣ የጥቅም ግጭት፣ የሥነ ምግባር ደነብ) ያላቸው ወይም በሁለት ወራት ውስጥ በሚሠጣቸው የቴክኒክ ድጋፍ አማካኝነት እነዚህን ሥርዓቶች ለማዘጋጀትና ለመፈጸም ቁርጠኛ የሆኑ
- ✓ ያመለከከቷቸውን ፕሮጀክቶች በቀጥታ ለማስተዳደርና ለመተግበር ሙሉ ኃላፊነት ሊውስዱ ይገባል፡፡ የተጠየቀውን የፋይናንስ ድጋፍ ለሌላ ሦስተኛ ወገን በመስጠት ፕሮጀክቱን ማስተዳደር አይፈቀድም፡፡

አስገዳጅ መስፈርት ባይሆንም ከሴቶች፣ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች ጋር የሚሰሩ አካላት እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ፡፡

7.3.4. የፕሮጀክት ሃሳቡ የሚቀርብባቸው ክልሎች

የሚቀርቡ የፕሮጀክት ሃሳቦች በማእከላዊ ኢትዮጵያ ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ ፣ ትግራይ ክልሎች እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በማህበረሰብ፣ በወረዳ፣ በዞን ወይም በክልል ደረጃ ሊከናወኑ የታሰቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱ አካባቢዎች ውጪ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ፈፅሞ ተቀባይነት የላቸውም፡፡

7.3.5. የማመልከቻዎች ብዛት

በዚህ የፕሮጀክት ድጋፍ የፍላጎት መግለጫ ማመልከት የሚፈልግ ማንኛውም ድርጅት ማመልከት የሚችለው አንድ ጊዜ ብቻ ለአንድ ክልል ነው፡፡ ከአንድ ማመልከቻ በላይ በአንድ ክልልም ይሁን በሌሎች ክልሎች የሚያመለክቱ ድርጅቶች ማመልከቻወቻቸው ሙሉ በሙሉ ውድቅ ይደረጋሉ፡፡

7.3.6. የፕሮጀክት ጊዜ

በዚህ የፕሮጀክት ድጋፍ የፍላጎት መግለጫ የሚቀርቡ የፕሮጀክት ሃሳቦች የጊዜ ቆይታ ቢያንስ አስራ ሁለት ቢበዛ ደግሞ አስራ ስምንት ወራት መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## 7.4. የማመልከቻ ሒደቶች እና የጊዜ ገደብ

አመልካች ድርጅቶች የፍላጎት መግለጫ ሠነዳቸውን በፍላጎት መግለጫ ማመልከቻ እዝል ወይም አባሪ 2 በቀረበው ፎርም መሠረት ማዘጋጀትና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ሁሉም አመልካቾች የማመልከቻ ፎርሙን በጥንቃቄ በመከተል ሁሉንም የማመልቻ ክፍሎች

በተሟላ መንገድ ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ አመልካቾች መመሪያውን ተከትለው የፍላጎት መግለጫቸውን በሚጠበቀው ልክ ማቅረባቸው ለሚደረገው ጥልቅ የማመልከቻዎች (ኢኦአይ) ግምገማ ስለሚረዳ በትኩረት ሊሰሩ ይገባል፡፡ በዚህ የፍላጎት መግለጫ ላይ አመልካቾች የሚያመለክቱት የፕሮጀክት ሃሳብ የሚያስፈልገው ጠቅላላ በጀት እንዲሁም የኦፕሬሽን እና የፕሮግራም ወጪ በመቶኛ የበጀት ዝርዝር በሚቀርብበት የማጠቃለያ ሰንጠረዥ ላይ በግልፅ ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ ዝርዝር በጀቱ የሚቀርበው ይህንን የፍላጎት መግለጫው ውድድር አልፈው ወደ ሚቀጥለው ደረጃ በሚሸጋገሩበት ወቅት ወይም ሙሉ የፕሮጀክት ሠነድ ወይም ፕሮፖዛል እንዲያቀርቡ በሚጠየቁበት ጊዜ ይሆናል፡፡

የፍላጎት መግለጫ ሠነዶች/ማመልከቻዎች በሚከተለው የኢሜል አድራሻ eucsfplusapplicationround2@christian-aid.org, መላክ ይኖርባቸዋል፡፡ በተለያየ ምክንያት በኢሜል ለመላክ የማይችሉ አመልካቾች የሚያቀርቡትን የፍላጎት መግለጫ እና አስፈላጊ ሠነዶች በታተመ መልክ በአካል ከቀነ ገደቡ አስቀድሞ ማቅረብ ይችላሉ፤ ለዚሁም በሚከተለው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ዝርዝር አድራሻ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ በኢሜል ለሚቀርቡ ማመልቻዎች ርእስ (ሳብጀክት) በሚለው ላይ **የአመልካቹ ድርጅት ስም** እንዲሁም የፕሮጀክት ሃሳቡን ለመተግበር ያሰበበት **ክልል** ሊጠቀስ ይገባል፡፡ አመልካቾች ሠነዶችን ለመላክ ማስፈንጠሪያ ወይም ሊንክ እንዳይጠቀሙ እንገልጻለን፡፡

***ሰንጠረዥ 1፡ ሰነዶችን በአካል ማቅረብ የሚቻልባቸው አድራሻዎች***

| **የድርጅቶች ስም** | **አድራሻ** | **ክልል** |
|---|---|---|
| *ሲቪል ሶሳይቲ ሪሶርስ ሴንተር* | አዲስ አበባ ቦሌ ክፍለ ከተማ በፍሬንድ ሺፕ ህንጻ ጀርባ አሌክስ ህንጻ አራተኛ ፎቅ የቤት ቁጥር 4 ሲ<br>**የሚመለከተው ኃላፊ፡** ሄኖክ ተሾመ,<br>ስልክ ቁጥር: +251974157421 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር |
| | ሆሳእና ከተማ፡ ማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ፋይናንስ ቢሮ፣ 2ኛ ፎቅ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት<br>**የሚመለከተው ኃላፊ፡** አቶ ኤፍሬም ሳሙኤል<br>ስልክ ቁጥር:+251 911 915142 | ማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል |
| *ክርስቲያን ኤይድ የጂንካ ጽ/ቤት* | የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ፣ ክርስትያን ኤይድ ጂንካ አካባቢ ጽ/ቤት ጂንካ ከተማ ፣ አርኪሻ ቀበሌ አክሽን ፎር ዴቨሎፕመንት ግቢ<br>**የሚመለከተው ኃላፊ፡** አቶ ነነፃት ፈለቀ,<br>ስልክ ቁጥር: 251 913 232 651 | ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል |
| *ጨራ አቡጊዳ የኪነጥበብ ማህበር* | መቀሌ ከተማ አዲ ሀቂ ክ/ከተማ ፣አዲ - ሀውሲ ቀበሌ በቅድስተ ማርያም ቤተክርስትያን አካባቢ በአዲ ገበያ አቅራቢያ<br>**የሚመለከተው ኃላፊ፡** አቶ ቢኒያም ናደው<br>ስልክ ቁጥር +251 914721453 | ትግራይ ክልል |

የፍላጎት መግለጫውንና ተጓዳኝ ሠነዶችን በአካል ለማስረከብ የሚፈልጉ አመልካቾች የማመልቻ ሠነዶችን ሁለት ኮፒ ከማመልከቻ መሸኛ ደብዳቤ እንዲሁም ከሁሉም አስፈላጊ ሰነዶች ጋር በኢንቨሎፕ አሽገው እንዲሁም በኢንቨሎፑ ላይ የድርጅቱን ማህተም መተው ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ እነዚህን ሠነዶች በሚያቀርቡበት ጊዜ አመልካቾች ማመልከቻቸውን

ማስረከባቸውንና በተቀባዩ ዘንድ መመዝገቡን ሊያረጋግጡ ይገባል፤ ለዚህም የተፈረመ እንዲሁም ቀን የሰፈረበት ማረጋገጫ ደብዳቤ ከተቀባዩ መ/ቤት መቀበል ይኖርባቸዋል፡፡

የማመልከቻ ሠነዱ ከሚከተሉት ደጋፊ ሰነዶች ጋር ሊቀርብ ይገባል፡፡

1. የድርጅቱ ህጋዊ የምዝገባ ሠነድ ወይም የምዝገባ ምስክር ወረቀት
2. የሶስት አመታት (2015-2017) ወይም (2023፣ 2024፣ 2025) ድርጅታዊ የኦዲት ሪፖርት (የቅርብ ጊዜ የፋይናንስ አቋምን በሚያመለክት መልኩ)
3. በአባሪ/ዕዝል-3 መሠረት የተሟላ የፕሮጀክት የፍላጎት መግለጫ ሠነድ
4. በአባሪ/ዕዝል-4 መሠረት (የተፈረመ እና ማህተም ያረፈበት) በማመልከቻው የተሰጡ መረጃዎችን ትክለለኛነት ማረጋገጫ (ዲክላሬሽን) እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች፡፡

**የማመልከቻ ጊዜ ገደብ**

የፍላጎት መግለጫው የማቅረቢያ የጊዜ ገደብ **ሀምሌ 28፡ 2018 ዓ.ም ከቀኑ 11፡00 ሰዓት** ነው፡፡ አመልካቾች የፍላጎት መግለጫ ማመልከቻዎቻቸውን/ሠነዶቻቸውን ከጊዜ ገደቡ አስቀድመው በማቅረብ ከከፍተኛ የኢንተርኔት ትራፊክ መጨናነቅና ሊያጋጥም ከሚችል የኤሌክትክ አገልግሎት መቆራረጥ ጋር የተያያዙ እክሎችን ወይም ተግዳሮቶችን እንዲያስወግዱ ይመከራሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሰው የማመልከቻ የጊዜ ገደብ በጥብቅ መከበር ይኖርበታል፡፡ ከቀነ ገደቡ በኋላ የሚቀርብ ማንኛውም ማመልከቻ/የፍላጎት መግለጫ/ ወይም ሠነድ ተቀባይነት የለውም፡፡

## የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

ለማንኛውም አይነት ቅሬታ አመልካቾች የክርስትያን ኤይድን የቅሬታ ማቅረቢያ ኢሜል Ethiopia.complaintsround2@christian-aid.org በመጠቀም ያጋጠማቸውን ቅሬታ ሊልኩ ይችላሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር በክልላዊ የማመልከቻ መቀበያ ማእከሎቻችን ውስጥ የቅሬታ ሰነዶችን በአካል ማቅረብ የሚያስችሉ የቅሬታ ማቅረቢያ ሳጥኖች ስለተዘጋጁ በዚያ ውስጥ ማስገባት ይቻላል፡፡

### 7.5. የማመልከቻዎች ግምገማ ሥርዓት

ማመልከቻዎቹ ከዚህ ቀደም በተቋቋሙ የፍላጎት መግለጫ ግምገማ ኮሚቴዎች አማካኝነት ይገመገማሉ፡፡ ሁሉም ማመልከቻዎችም ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ በሶስተኛ ወገን የፋይናንስ ድጋፍ መመሪያ ላይ በተገለጹ ውስጣዊ ሂደቶችና መስፈርቶች አማካኝነት ይገመገማሉ፡፡ የማመልከቻ ግምገማ ውጤት አመልካቹ በፍላጎት መግለጫ መመሪያው ክፍል 7.1 ላይ የተመለከቱ መሟላት የሚገባቸውን የብቁነት ግደታ መስፈርቶች ያላሟላ ከሆነ፣ ማመልከቻው ወደቀጣይ ቴክኒካዊ ዝርዝር ግምገማ ሒደት መሔድ ሳያስፈልገው በዚህ ብቸኛ ምክንያት ውድቅ የሚደረግ ይሆናል፡፡

### 7.6. የፍላጎት መግለጫ አስተዳደራዊ ግምገማ

በአስተዳደራዊ ግምገማ ላይ የሚከተሉት ጉዳዮች ይገመገማሉ፡፡

- የማመልከቻው የጊዜ ገደብ፡፡ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ያልተላኩ ማመልከቻዎች ወደሚቀጥለው ፕሮሰስ ሳይሄዱ ውድቅ ይደረጋሉ፡፡

- የፍላጎት መግለጫው ሁሉንም በዚህ የፍላጎት መግለጫ ማመልከቻ መመሪያ ላይ የተቀመጡ የብቁነት መስፈርቶችን እንዲሁም በፍላጎት መግለጫ ማመልከቻ ቅጹ ላይ የተመላከቱትን መመሪያዎች ማሟላት አለበት፡፡ ማንኛውም እንዲቀርብ የተጠየቀ መረጃ ከጎደለ ወይም ከተሳሳተ ፣ ማመልከቻው በዚህ ምክንያት ብቻ ውድቅ ይደረጋል፤ ወደ ቀጣይ ዝርዝር የግምገማ ሒደትም አይገባም፡፡

## 7.7. የፍላጎት መግለጫ ዝርዝር ግምገማ

የፍላጎት መግለጫው ሠነድ የአስተዳደራዊ ግምገማ መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ ወደ ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ ሒደት እንዲገባ ይደረጋል፡፡ የፍላጎት መግለጫው ሠነድ ግምገማ የሚካሔደው ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ  የተመለከቱ ዝርዝር መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ሲሆን የግምገማው ውጤት ከመቶ የሚሠላ ይሆናል፡፡

| **የግምገማ መስፈርቱ መግለጫ** | **የተሰጠው ክብደት** |
|---|---|
| ማመልከቻው በፍላጎት መግለጫ ሠነድ ዝግጅት መመሪያው ላይ ቅድሚያ ከተሰጣቸው አላማዎችና ሁኔታዎች አንፃር ምን ያህል አግባብነት አለው? | 10 |
| የፕሮጀክት ሃሳቡ አጠቃላይ እና ዝርዝር አላማዎች በግልጽ ተመላክተዋልን? | 10 |
| የውጤቶች ማእቀፍ (ሬዛልትስ ፍሬምዎርክ) የተዋቀረበት መንገድ ዝርዝር ሥራዎች ወደ ውጤቶች የሚያመሩበት እና ውጤቶች ደግሞ ፕሮጀክቱ በሚጠናቀቅበት ወቅት ይደረስበታል ተብሎ ለሚጠበቁ ቁልፍ ውጤቶች አስተዋጽኦ በሚያበረክቱበት መንገድ ነውን? | 20 |
| የታቀደው የፕሮጀክት ሃሳብ በዝርዝር የተመለከቱ ችግሮችን፣ ማነቆዎችን እና ተግዳሮቶችን ከመፍታት አንፃር ምን ያህል አግባብነት አለው? | 10 |
| የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች በሚገባ ተለይተዋልን? ልየታው ወይም መረጣው የተካሔደው ስልታዊ በሆነ መንገድ ነውን?  እነዚህ ተጠቃሚዎች ያለባቸው ማነቆዎች፣ ተግዳሮቶች እና ዋና ዋና ፍላጎቶች (እንደ መብት ባለቤቶች እና/ወይም ሃላፊነት ተቀባዮች) በግልጽ ተለይተዋልን? ከአውሮፖ ህብረት ሲ. ኤስ. ኤፍ ፕላስ አላማዎች ጋር የተናበቡ ናቸውን? | 10 |
| የፕሮጀክቱ ባለድርሻ አካላት በግልጽ ተለይተዋልን? ለባለድርሻ አካላቱ አስፈላጊው ዝርዝርስ ተዘጋጅቷልን? አመራረጡስ ስልታዊ በሆነ መልኩ ነውን? ከአውሮፓ ህብረት ሲ. ኤስ. ኤፍ ፕላስ ፕሮግራም ተጠቃሚ አካላት ጋርስ ተመሳሳይነት አላቸውን? | 10 |
| የፕሮጀክት ትግበራ ሥጋቶች ተዘርዝረዋልን? አግባብነት ያላቸው የስጋት አመራር ዘዴዎች ቀርበዋልን? | 5 |

| **የግምገማ መስፈርቱ መግለጫ** | **የተሰጠው ክብደት** |
|---|---|
| አመልካቹ ድርጅት ያቀረበው ልምድ/ተሞክሮ ካመለከተበት ዘርፍ/ሴክተርና ከአውሮፓ ህብረት የሲ. ኤስ. ኤፍ ፕላስ ፕሮግራም የትኩረት አቅጣጫዎች በምን ያህል ደረጃ የተናበበ ነው? *ይህ መስፈርት በመነሻ ደረጃ ላይ የሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት አመልካቾችን አይመለከትም።* | 15 |
| አመልካቹ ያቀረበው የበጀት መጠን የፍላጎት መግለጫ መመሪያው የተቀመጠውን ጣሪያ ያሟላልን? አስገዳጅ መስፈርቶችንስ ያሟላልን? | 10 |
| **ድምር** | **100** |

ወደ ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ የተካተቱ የሁሉም አመልካቾች የፍላጎት መግለጫ ሠነዶች ከተገመገሙ በኋላ በአጠቃላይ ውጤት መሰረት ለአመልካቾች ደረጃ የሚሰጥ ይሆናል። በተሰጠው ደረጃ መሠረት የተመረጡ ድርጅቶች ሙሉ የፕሮጀክት ሠነድ ማዘጋጀት የሚያስችላቸውን ሥልጠና እንዲወስዱ የደረጋል። በቀጣይነትም ከሥልጠናው ያገኙትን ክህሎት በመጠቀም ሙሉ የፕሮጀክት ሠነድ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡና እንዲወዳደሩ ይጋበዛሉ።

***ማሳሰቢያ፡*** ***በዚህ መመሪያ በተለያዩ ቋንቋዎች መካከል ማለትም እንግሊዝኛ፣ አማርኛና ትግርኛ የትርጓሜ/ማንኛውም ዓይነት የሃሳብ ግጭቶች/ ቢያጋጥሙ የእንግሊዝኛው ትርጉም/እትም/ ገዥ ይሆናል።***

------------//----------------